# 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ'፤ በዙሪያ-ጥምጥም ችግሮች ላይ "የሕገ-መንግሥት" ቀውስ ሲታከል!

## <u>የዜጎችን አንድነትና እንደ-ሕዝብ በጋራ መቆምን የግድ የሚል ዳግም የፈተና ጊዜ፤</u>

*የግል አስተያየት፡- በአያል ሰው ደሴ - ሐምሌ ፲ ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ/ም*

ከሁሉ በፊት የዚኽ አጭር ጽሑፍ ዓላማ መነሻው የአቶ መለስ ዜናዊን የጤንነት ሁኔታ የተመረኮዘ ይሁን እንጂ ስለ ጤንነታቸው ይዞታም ሆነ እሣቸው ላይ ያተኮረ እንዳልሆ ይታወቅልኝ፡፡

የሕወሓቱ የዕድሜ-ልክ መሪና ላለፉት ሃያ-አንድ ዓመታት በኢትዮጵያ አገራዊ ሥልጣን ቁንጮ ሆነው የቆዩት አቶ መለስ ዜናዊ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ ለሕይዎታቸው ያሰጋ ከፍተኛ የጤና መታወክ የደረሰባቸው የመሆኑ ዜና ከተሰማ ጀምሮ የኅብረተሰባችን ዋነኛ የመወያያ ርዕስ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የአቶ መለስን የጤና ሁኔታ ከራሣቸው፣ ከፈጣሪያቸውና ከቅርብ ሐኪሞቻቸው ውጭ በትክክል የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ የጤንነታቸው ሁኔታ በሕይዎት-ካለመኖር-እስከ-አገግሞ-ድንገት-ብቅ-እስከ-ማለት ሊያደርስ መቻሉ፣ ወይንም በሕይዎት ኖረውም በሥራ-ገበታቸው ላይ ለመሠለፍና እስካሁን ተቀናቃኝ በሌለው መልክ ይዘውት የቆዩትን ሙሉ የሥልጣን ኃላፊነት መወጣት የማይችሉ "የቁም-ሙት" ሊያደርጋቸው ይችልም እንደሆነ በበኩሌ አላውቅም፡፡ የጤናቸው ሁኔታ ምንም-ይሁን-ምን ግን የገጠማቸውን የጤና መታወክ ተከትሎ ዜጎችን የምር የሚያሣስቡ ጥያቄዎች መነሣታቸው የግድ ሆኗል፡፡

ሰብዓዊ ተፈጥሮ ያለው ሁሉ ዓለማዊ ሂደቱን ጨርሶ መለየቱ ያለና ለማንም የማይቀር ፅዋ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አቶ መለስ ዜናዊም መቼም-ይሁን-መቼ ከዚኽ ተፈጥሮኣዊ ግዴታ ሊያመልጡ እንደማይችሉ አጠያያቂ አይደለም፡፡ በሕዝብ ዘንድ በበጎ ይታዩም አይታዩ፣ በአንድ አገር ላይ ሙሉ ቁጥጥርና ወሣኝነት ያላቸው ግለሰብ መሪዎች ጤና ማጣት ትኩረትን የሚስብና አነጋጋሪ መሆኑ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ይኽ ደግሞ እንደ አፄ ምኒልክ በሕዝብ ዘንድ "እምዬ" የመባል ፀጋን የተጎናፀፉ፣ አፍቅሮተ-ሕዝብን ያተረፉና "ሸሕ ዓመት ያንግሥልን" የሚባሉም ይሁኑ፤ በአብዛኛው የሕዝብ ምሬትንና የማያባራ እርግማንን ያተረፉትን ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም መሪ ለአንድ አገርና ሕዝብ የሚያደርገው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይበልጥ የሚለካውና የሚመዘነው በሥልጣን ላይና በሕይዎት እያለ በሚያደርገው ከመሆን ይልቅ ሥልጣን ሲለቅ ወይም በሕልፈተ-ሕይዎት ሲሰናበት ትቶትና ተክቶት በሚሄደው የሥርዓት ዓይነት ነው፡፡ አንዳንዶች በሥልጣን ዘመናቸውና በሕይዎት እያሉ ካደረጉት በተጨማሪና እንዲያውም ይበልጥ ካለፉ በኋላ በሞታቸው አገርንና ሕዝብን የሚታደጉና በሠሩት ሥራና በተዉት ቅርስ ዝንት-ዓለም ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡ በአንፃሩ ሌሎች በሥልጣን ዘመናቸው ለሕዝብ ሣይመቹ መኖራቸው አልበቃ ብሎ ሲያልፉ ጦስ ትተው ይሄዳሉ፡፡ ለዚኽም ነው ማንም መሪ በሥልጣን ዘመኑ ለአገርና ለሕዝብ በሠራውና ተክቶት በሚሄደው ሁኔታ መለካት የሚኖርበት፡፡

በሥልጣን ዘመናቸው በግፍ ሥራቸው የሚወቀሱ፣ ሕዝብን በመበደልና አገርን በመጉዳት የሚታወቁ የአገዛዝ መሪዎች በማይቀረው ተፈጥሮኣዊ ኅልፈት ከመሰናበታቸው በፊት ግን በአገራቸው ላይ ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮ በነፃ ፍርድ ቤትና በሕዝባቸው ፊት ለሠሩት ሁሉ ተጠያቂ ቢሆኑና ሕዝብ ፍትኅን ቢያገኝ ለአገርና ለቀጣይ ትውልዶች መሰል የሌለው ትምሕርት ይሆንናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ይኽ ቢሆን በአገራችን የፍትኅ ሥርዓትን ለማረጋገጥና የአምባ-ገነን አዙሪትን ለመስበር የሚደረገውን ጥረት በጣሙን ያግዛል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም በበኩሌ ለኮሎኔል መንግሥቱም ሆነ ለአቶ መለስ ወይም ከነሱ ተመሣሣይ ለሆኑ የአገዛዝ መሪዎች ተፈጥሮ ብይኗን ከምትሰጣቸው ይልቅ የምመኘው ይኽንኑ ምድራዊ የፍትኅ ሂደት ነው፡፡

በቁም ያልተመቸችውንና ያስቸገረችውን "ቆመሽም ገደልሽኝ፣ ሞተሽም አልተውሽኝ" አለ እንደተባለው የአገር-ሰው ሆነና የአቶ መለስን ጤና-መታወክ ታክኮ ያለው የአገራችን ሁኔታ የሁሉም መነጋገሪያ የሆነበት ምክንያት የግድ ስለሣቸው ጤንነት በመጨነቅ ሣይሆን አገራችን ምሬትና ብሶት የበዛበት፣ ኑሮ ያንገፈገው፣ ለውጥን የሚናፍቅና ተስፋው የጨገገበት ሕዝብ ቋፍ ላይ ባለበት፣ ጎሣንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ አደገኛ ውጥረቶችና እነሱንም የሚያራግቡ የተደራጁ ኃይሎች ባሉበት፣ የአገሪቱን ሰላም ለመበጥበጥና ሁኔታዎችን ለማባባስ እጃቸውን ለማስገባት ወደ-ኋላ የማይሉ የውጭ ኃይሎች ባልገደዱበትና ከሁሉም በላይ አስተማማኝ የተዘጋጀ ተተኪ አገር-አቀፍ ኃይል በሌለበት ቀውስን-ያረገዘ ዙሪያ-ጥምጥም የውጥረት ክምችት ውስጥ ስለምትገኝ መሆኑ ግልጥ ነው፡፡ እነኝኽ እያንዳንዳቸው በተናጠል የማንኛውንም አገር ኅብረተሰብ ወደ ከባድ ትርምስ ሊወስዱ የሚችሉ የቀውስ ምንጮች አንድ-ላይ ተዳምረው በአንድ-ወቅት መከሰታቸው ሁሉንም ቢያሣስብ የሚገርም አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያዊያንን እያሳሰቡና አልፎም የስጋት ምክንያቶች የሚሆኑት በአጭሩ የሚከተሉት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

*1ኛ. በብሔራዊ አለኝታነት ሊታይ የሚችል፣ በሕዝብ ዘንድ ተኣማኒነትና ተቀባይነት ያለው አገር-አቀፍ አካል (ድርጅት) ወይም ተቋም አደገኛ ክፍተት፤*

የአገራችን የወቅቱ ሁኔታ በብዙዎች ዘንድ ከፍተኛ ስጋትና በወደፊቱ ዕጣ-ፈንታ ላይ እርግጠኛ ያለመሆን ስሜት እንዲሰፍን ካደረጉት ምክንያቶች ዋናው ሁነኛ፣ አስተማማኝና ተኣማኒነት ያለው ብሔራዊ (አገር-አቀፍ) ተለዋጭ ኃይልም ሆነ ቢያንስ ተቋም ያለመኖሩ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚኽ ደግሞ ምንጩም ተጠያቂውም በአንድ በኩል አገዛዙ የተከተላቸው የእመቃና የአፈና ፖሊሲዎች የፈጠሩት ሁኔታና በሌላ በኩል ለሥርዓት ለውጥ በሚታገለው ክፍል ቅጥ-ያጣና የተዝረከረከ አካሄድና አሠላለፍ ጣምራ እክሎች መሆኑ ይመስለኛል፡፡

በዚኽ ዙሪያ ቀደም-ሲል በ'*ወገናዊ ጥሪ*' መልክና በሌሎች አጋጣሚዎች ብዙ ብዙ ያልኩበት ስለሆነ እዚኽ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ ምንም እንኳን በአገር-ውስጥም ይሁን ከአገር-ውጭ በአንዳንድ ታጋይ ወገኖች ዘንድ የተለያዩ የመሰባሰብ ኅራዎች ቢኖሩና ጥረቶች የቀጠሉ ቢሆንም፣ አሁንም ለክፍተቱ አስተማማኝ ምላሽ እንዳልተገኘለት ግልጥ ነው፡፡ አገር-አቀፍ አሰባሳቢና ተስፋ-ሰጪ ብሔራዊ አለኝታ በሌለበት ሁኔታ ብሶት የበዛበትና የተማረረን ኅብረተሰብ ወደ-ተለያዩ አፍራሽ አቅጣጫዎች ለመኅተት ብዙ ቁጥር ያለው ኃይል እንደማያስፈልግ ይታወቃል፡፡ የወደፊት ዕጣ-ፈንታውና መጪው ሁኔታ ላይ ምንም ዓይነት እርግጠኛነትም ሆነ ዋስትና የሌለው ምልዓተ-ሕዝብ በተደራጁ ጥቂቶች ሰላሙን፣ መረጋጋቱንና አንድነቱን ሊያጣ እንደሚችል በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው፡፡

ይኽ አደገኛ ክፍተት ባለባት አገራችን ላይ የአቶ መለስ የጤና ይዞታ ሊፈጥር ከሚችለው የዋለለ ሁኔታ ሲጨመር ሊከሰት የሚችል ቀውስን-ያረገዘና ስጋት ላይ የሚጥል ያልተረጋጋ ክስተት ምናልባታዊነቱ ጎላ ብሎ ቢታይና ብዙዎችን ቢያሣስብ ሊገርም አይገባም፡፡
አገር-ወዳዱንና ዴሞክራቱን ለውጥ-ፈላጊ ክፍል በአገዛዙ መኻል ሊከሰት በሚችል የውስጥ ሽኩቻም ሆነ በሌሎች ሰበቦች ይደርሳል ብለን የምንሰጋበት ዋናው ምክንያት በሁኔታዎች ላይ ቁጥጥር ስለሌለን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ምን-ጊዜም ቢሆን ሁኔታዎች ላይ ጫና ለማሣደርና አቅጣጫ ለማስያዝ አቅም መገንባት እስካልተቻለ ድረስ በወደፊት ዕጣ-ፈንታችን ላይ ቁጥጥር ሊኖረን አይችልም፡፡

ለአገዛዙ ዕድሜ ማጠርም ሆነ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሣኙ የአቶ መለስ ጤና መሆን-አለመሆን ወይም በሕይዎት መኖር-አለመኖር፣ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መኻል ክፍፍል መኖር-አለመኖር፣ ወዘተ ሣይሆን ሕዝብን መልሶ የትግሉ ማዕከልና የመፃዒ-ዕድሉ ወሣኝ እንዲሆን ሁኔታዎችን ሊያመቻች የሚችል፣ ተኣማኒነትና አገር-አቀፍ ተቀባይነት ያለው ጠንካራና መሠረተ-ሠፊ ብሔራዊ ኃይል ሲኖር መሆኑ በሚገባ ሊጤን ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት ቁም-ስቅሉን እያየ ባለበት ሁኔታ ከዳር-ዳር አንድ-ላይ በመነሣትና በማመፅ መብቱን ከማስከበር የተገታው ከሚገርም ቻይነቱና ትዕግሥቱ ጋር ካሉ ዋና-ዋና ምክንያቶች መኻል "ከዚያ በኋላስ?" ለሚለው ለወደፊቱ ዋስትና ጥያቄ በቂና ተግባራዊ ምላሽ ሊሆን የሚገባው የዚኽ የሁነኛ ተተኪ ክፍተት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የዚኽ ክፍተት ደግሞ በገኸርው ክፍል ባኅሪ ላይና በሚከተለው የወደፊት አቅጣጫ ላይ ያለውና የሚኖረው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ስለሆነም ነው አሁንም ቢሆን በለውጥ-ፈላጊው ታጋይ ክፍል በኩል ጉዳዩ የቅድሚያ-ቅድሚያ ሊሰጠውና ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልገው ሊታወቅ የሚገባው፡፡

*2ኛ. የመብቶች መረገጥ፣ አጠቃላይ አፈናና የኑሮ ውድነት የወለዳቸው ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮች፣ ብሶቶችና ተስፋ-መቁረጥ ለነውጥ የተመቻቸ ሁኔታ፤*

ብሶት የበዛበት፣ የተበደለና የተጨቆነ ሕዝብ ውሎ-አድሮ መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ በተለይ የአቶ መለስን ጤና ተከትሎ በገኸርው ሠፈር ሊኖር የሚችል የውስጥ እክል ወይም አዝማሚያ ለመነሣሣቱ አደፋፋሪ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በበኅ ጊዜ ይኽ ሕዝብን ለመብቱ መነሣሣት ጋባዥ የሆነ ሁኔታ አስጊ ሆኖ መታየት ሣይሆን እንዲያውም እንዲመጣ ጥረት የሚደረግበት ጉዳይ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ የብዙዎች ጭንቀት ግን ሕዝብ ለመብቱ መነሣቱ ላይ ሣይሆን ከላይ በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው የብሔራዊ አለኝታና ምትክ በሌለበት ሁኔታ መነሣሣቱ አንድነት የጎደለው፣ የተበታተነና እየተነጠለ በየተራ ሊመታ የሚችልና ሕዝብን የባሰ ጨለምተኝነት ውስጥ የሚከት ከመሆንም አልፎም በተለይ ጎሣና ሃይማኖትን መሠረት ላደረገ ሕዝብን ለአሰቃቂ የእርስ-በርስ ትርምስ የሚዳርግ ሁኔታን ሊፈጥር የመቻሉ ምናልባታዊነት ነው፡፡ ይኸም የሚሆንበት ምክንያት

በዚኽ እጅግ የጠነከረ የሕዝብ ብሶት ሣቢያ የሚፈጠር ማንኛውም የማዕከላዊነት ክፍተት ከማንም በላይ ለለየላቸው አክራሪዎችና ፀረ-አንድነት ኃይሎች እጅግ አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥር ነው።

ማዕከላዊነት ያጣና ስብጥርጥሩ የወጣ የነውጥ ሁኔታ፤ በተለይ ሃይማኖትና ጎሣን የመሣሰሉ ሕዝብን እርስ-በርስ ለማናከስና ወደ-ትርምስ ለመውሰድ ስሜታዊነትን በቀላሉ ለማስፈን የሚያስችሉ ከፋፋይ መሥመሮችን ለመግፋት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በአገራችን ደግሞ ሁለቱም መሥመሮች በተቀነባበረ መልክ ረዘም ላለ ጊዜ እየተገፉ መቆየታቸውና በሕዝብ መኻል የቆዩ የትሥሥር አውታሮች እንዲሸረሸሩ መደረጉ ነው ስጋቱን ጠንከር የሚያደርገውና ይበልጥ አሣሳቢ የሚያደርገው።

## *3ኛ. የአቶ መለስን ከዋና የሥልጣን መድረክ ላይ አለመኖር ተከትሎ የሚፈጠር በገዥው ክፍል መኻል የሚከሰት ባለ-ብዙ-ፈርጅ የሥልጣን ሽኩቻ፤*

ይኽ ጉዳይ ከስሜታዊነትና ከ'በይሆናል' ግምት ውጭ ከድርጅቱ ተፈጥሮ-ባኅሪ፣ ከሚመሩት ሰዎች ዓይነትና በመስክ ላይ ካለው አጠቃላይ ሁኔታ አኳያ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ይመስለኛል። እዚኽ ላይ የኢሕአዴግን አውራ ድርጅት የሕወሓትን አደረጃጀትና የመሪዎቹን ባኅሪና ታሪክ ለሚያውቅ ለዚኽ ጉዳይ ብዙ ክብደት ላይሰጠው ይችላል። በበኩሌ አቶ መለስ ሥልጣን ላይ መሆን-አለመሆን ወይም በሕይዎት መኖር-አለመኖር የድርጅቱን መሠረታዊ ባኅሪና ይዞታ ይኸንን ያኽል የሚቀይረው አድርጌ አላየውም። በተለይም በቁጥር አንድ ላይ ለተጠቀሰው አደገኛ ክፍተት የማያወላዳ ምላሽ እስካልተሰጠ ድረስ ድርጅቱ እንደ-ድርጅት ይቀጥላል።

የሆነ-ሆኖ የሥልጣኑ ሽኩቻ ሦስት ዘርፍ ሊኖረው ይችላል። አንዱ በሕወሓት የበላይ አመራር መኻል፣ ሁለተኛው በሠራዊቱና በፀጥታው መዋቅር ውስጥ እና ሦስተኛው በሕአዴግ አባል ድርጅቶች መኻል፤ በተለይም በአውራው ድርጅት በሕወሓትና በቀሩት መኻል።

በሕወሓት አመራ በኩል ሊኖር የሚችለውን ሽኩቻ መልክ የሚያስይዘውም ሆነ መልስ የሚሆነው በሁለተኛው (በሠራዊቱ ውስጥ) ያለው ይዞታ ይሆናል። በተለይ የውጭ አጋሮቻቸው ዋና ትኩረት በአንድ በኩል እንደ ቻይናና ሕንድ የመሣሰሉ ብዙ መዋዕለ-ንዋይና ጥሪት-አፍሣሾች ጥቅማቸውን ለማስከበር ያለው ይዞታ ሣይናጋ እንዲቀጥል ከመፈለግ፣ በአብዛኛው በምዕራቡ ዓለም (በተለይ አሜሪካና እንግዚዝ) በኩል ደግሞ በአፍሪቃ-ቀድ አካባቢ ሰላምና መረጋጋት" እንዲኖር ካለ ፍላጎትና ለዚኽ ደግሞ ኢትዮጵያ ከአላት ቁልፍና "ምትክ-የለሽ" ሚና አኳያ አገሪቷ የውስጥ መናጋት እንዳይደርስባት ሠራዊቱ "የማረጋጋት" ሥራውን በብቃት እንዲወጣ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ማንኛውም ቀጣይ መንግሥት ይኸንን "ኃላፊነትና ተልዕኮ" እንዲወጣ የሚቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

በሕወሓት አመራር መኻል ከአሥራ-ሁለት ዓመታት በፊት ከተከሰተው ልዩነት ወዲኽ በቀሩት የድርጅቱ አመራ አባላት ዘንድ አቶ መለስ ሊቆጣጠሩት ያልቻለ የጎላ ልዩነት አልነበረም ማለት ይቻላል። አንዱ በሕወሓት አመራር መኻል ሲብላላ የቀጠለ የልዩነት መሥመር የሚሆነው "በኤርትራዊትና በትግራዋይነት" ፍረጃ ሲሆን በተለይ አቶ መለስ የዚኽ "የበላይ ጠባቂና ዋና ተጠሪ" ሆነው ሲታሙ የቆዩ ስለሆነ፤ ምናልባት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የበላይነቱን የመቆጣጠሩ ጉዳይ አነታራኪና ሊያጋጭ ይችል ይሆናል።

በወታደሩ ይሁን በሲቪሉ የመንግሥት መዋቅሮች ላይ ያሉ ኃላፊዎች ሁሉ የበላይ የሌለባቸው ሿሚም፣ ሻሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ መለስ ስለሆኑ፣ ለእነዚኽ ሰዎች የሥልጣን መሠረት እሣቸው ናቸው። በማኪያቬሌያዊ ቅኝታቸውና ምግባራቸው የሚታወቁት አቶ መለስ ሥልጣናቸውን ለማደላደልና በእሣቸው ላይ አድማ እንዳይኖር በጋብቻና በልዩ-ልዩ የጥቅም መያዣ እንዲሁም በእሣቸው ላይ ጭፍን አመኔታ ባሏቸው ተከታዮቻቸው መኻል አለመተማመን እንዲኖር አድርገው ማቆላለፋቸው ይታወቃል። አንዳንዶቹም አቶ መለስን የሚያዩአቸው ለያዙት ሹመትና ላካበቱት ንብረት ብቻ ሣይሆን ለሕይዎታቸው ሣይቀር ዋስትናቸው አድርገው እንደሆነ ይነገራል። ጥያቄው እንግዲኽ የድርጅቱ አባላት በተለይ አመራሩ በችግር ጊዜ አንድ-ላይ መምጣት ልምዱና ባኅሪው እንዳለ ሆኖ፣ እነኚኽን ሙጫ ሆነው ያቆዩ ባለ-ሙሉ-ሥልጣን ግለሰብ ሙሉ-ቁጥጥር ሊኖራቸው የማይችሉበት ሁኔታም ሆነ በሕይዎት ያለመኖር ዕጣ ሲገጥማቸው ያ ከላይ የሚታይ የአንድነት ትሥሥር ምን ያኽል የደነደነና እስከ-መቼስ ሊቀጥል ይችላል? የሚለው ይሆናል። በእርግጥ የዚኽ ገዥ ቡድን አባላት በያዙት የፖለቲካ ሥልጣን አማካይነት አንዱ-ከሌላው የተያያዘበትና የአንዱ "ከጨዋታው ውጭ መሆን" የሌላውን የሚያናጋ የጥቅም ትሥሥር አለ። ይኽ ትሥሥር በጥንቃቄ ተይዞ በ"አብረን እንደያዝን አብረን እናጣለን" ዓይነት አብሮ የመቀጠል ፍላጎት ይኖራል።

ለዚኽ ገዢ ቡድን አባላት አብሮ ለመቆም የሚረዳቸው አንደኛውና እርግጠኛው ዘይቤ ግን "ሊያጠፉን ነው" የሚለውን ጠባብ ቅኝት ማቀንቀን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። የዚኽ ቅኝት አሣዛኙና አስቀያሚ ገፅታው ግን ይኽ ቅኝት በቡድነኝነት መንፈስና ስሜት ላይ ብቻ የሚቆም

ሣይሆን የትግራይን ሕዝብ ዳግም መጠለያና ከለላ ለማድረግ “በትግሬና በፀረ-ትግሬ” አደገኛና ኃላፊነት የጎደለው ጎሣዊ ፍረጃ እንዲሆን ሊደረግ የመቻሉ ጉዳይ ነው።

በአገዛዙ መዋቅር ውስጥ ላሉትና የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለሆኑት ክፍሎች የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጤና መታወክ አሣሳቢ የሚሆንባቸው ሥርዓቱ ሳይቋረጥና መሠረታዊ መናጋት ሳይደርስበት እንዲቀጥል ካለ ፍላጎት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ የገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ (በተለይም የአውራው ድርጅት ሕወሓት) አባላት ደግሞ በተቻላቸው መጠን ሥርዓቱ እንዲቀጥል ጥረት እንደሚያደርጉና ለተወሰኑትም የሞት-ሽረት ጉዳይ አድርገው እንደሚያዩት አጠያያቂ አይሆንም። የተወሰኑት ደግሞ ጉዳዩን ከአገር ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ከሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም አኳያ ሊያዩት እንደሚሞክሩና በዚኽም ረገድ “ከክበቡ” ውጭ ካሉ ወገኖች ጋር የጋራ አገራዊ መፍትኄ መሻቱን ለማስተናገድ የሚከጅሉና የሚሞክሩ ሊኖሩ ይችላሉ። እጅግ ከፍተኛ ድፍረትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ስለሚሆን የእምነት ተገዥ በሆነ ጠንካራ አገር-ወዳድ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች መመራት ከቻለ፣ ከሁሉም የክፍፍል መሥመሮች የአገሪቱን ዕጣ-ፈንታ በጎ አቅጣጫ ለማስያዝና አዎንታዊ ሚና ሊኖረው የሚችል ይኸኛው ክፍል ነው።

ጥቂቶች ደግሞ የአገሪቱን የውጥረት ሁኔታ፣ የሕዝብን አጠቃላይ ምሬትና ለለውጥ መነሳሳት በመገንዘብ፣ አገዛዙም በነበረበት ይዞታ መቀጠል የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በማጤን የተወሰኑ ጥገናዊና ይስሙላዊ ለውጦችን በማድረግ ኢሕአዴግን “በተኃድሶ” ለማስቀጠል ማሰባቸው አይቀርም። በዚኸኛው መስመር በተለይ የውጭ አጋዦቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ፍላጎትም ግፊትም ሊኖር መቻሉን መገመት ይቻላል። እነዚኽ ባዕዳን ቅድሚያ የሚሰጡት ነውጥና የቀውስ አዙሪት የተጠናወተውና ያልተለየው የአፍሪቃ-ቀንድ አካባቢ ሰላምና መረጋጋት ለሚሉት ቁልፍ ጥያቄ በመሆኑና ለዚኽ ደግሞ ኢትዮጵያ ከአላት “ምትክ-የሌለው” ተፈላጊነትና ሚና አኳያ እንደሚሆን ግልጥ ነው።

በአቶ መለስ ጤና ምክንያት በተለይ በሕወሓት መኻል ሊኖር የሚችልን የሥልጣን ሽኩቻና ልዩነት ጎልቶ መውጣትም ሆነ “የውስጥ መፍትኄ” እንዲያገኝ የሚያደርገው በተለይ በለውጥ ፈላጊው በኩል የሚኖረው ጥንካሬ፣ አቀራረብና አጠቃላይ ይዞታ ይመስለኛል። የድርጅቱ መሪዎች ብቻ ሣይሆኑ በአባሎቻቸውም ዘንድ በችግር ጊዜ አብሮ የመቆምና “ገመናን የመሸፈን” ባኅል ከመኖሩ ሌላ በአንዳንዶቹ በኩልም ያለውን ሥርዓት “መናጋት” በተጣመመ መልኩ “ከኅልውና ዋስትና” ጋር አያይዘው ስለሚያዩት <u>ቀጣዩ ላይ በሚኖር አጉል ስጋት</u> ምክንያት እስካሁን ልዩነት አለን የሚሉትን ሣይቀር የሚያጠጋጋ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል። ስለሆነም በአንድ በኩል ከማንምና ከሁሉም በላይ የጋራ አገራችን አንድነት፣ ሰላምና መረጋጋት የሁሉም ኢትዮጵያዊ (የመንግሥት ሥልጣን የያዘውም ይሁን ለሥርዓት-ለውጥ የቆመው ወገን) ጉዳይ መሆኑና እነዚኽም በገዥው ክፍል ብቻ የሚረጋገጡ እንዳልሆኑ ሁሉም እንዲረዳው ማድረግ ያስፈልጋል። ትግሉም ሁሉም ተጠቃሚ ለሚሆንበት የሥርዓት ለውጥ እንጂ በማንም ቡድን ወይም የሕዝብ ክፍል ላይ የተቃጣ እንዳልሆነ፣ እንዲመጣ በሚፈለገው የሥርዓት ለውጥ ላይ ማናቸውም የሚሰጉበት ምክንያት እንደሌላቸው “ማስተማመኛ” ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ማወቁ ተገቢ ይመስለኛል።

አንዳንዶቹ፤ በተለይም በአጉል ዕብሪት የተወጠሩና የአገርን ዘለቄታዊ ጥቅም ሣይሆን ጊዚያዊውንና የቅርቡን የሚያዩ ክፍሎች፤ ያለውንም ሆነ ማንኛውንም የቀውስ ሁኔታ በመጠቀም “በአገር ሰላምና መረጋጋት” ስምና ሽፋን የሚደፈጠጠውን ደፍጥጠው ተጠናክሮ ለመውጣትና የሥልጣን ይዞታቸውን እንዳለ ለማስቀጠል የሚያስቡ እንደሚኖሩ ጥርጥር የለውም። በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩን ሆን-ተብሎ በማወላገድ ትግሉ “በትግሬና በፀረ-ትግሬ” እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ “እንዳያጠፉን-አብረን-እንቁም” በሚል በጠባብ ጎጠኝነትና ቡድናዊ ስሜት ወደ-ውስጥ የማየትና የመሰባሰብ ሙከራ በማድረግ የድርጅት የበላይነትን ለማስቀጠል የሚደረግ ሙከራ ሊኖር ይችላል። ሆኖም ሁለቱም መሥመሮች አጉልኛ፣ ዘለቄታዊነት የሌላቸው፣ በዴሞክራሲ፣ በፍትኅ፣ በእኩልነትና በአንድነታችን ኪሣራ እንደሚሆን ሊታወቅ ይገባል።

በዚኽ የሥልጣን ክፍተት ሣቢያ በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መኻል የሚነሣ ልዩነት እርቀት ላይሄድ ይችላል። ለዚኽ ደግሞ ዋናው ምክንያት በነዚኽ አባል ድርጅቶች የአመራር ቁንጮ ላይ ያሉት የአውራው ድርጅት ጉዳይ አስፈፃሚ፣ እንባ ጠባቂና አልፎም “ከጳጳሱ-ቄሱ” ዓይነት ተስፈንጣሪ-ታማኝ በመሆናቸው ነው። ሆኖም ግን በእነዚኽ ድርጅቶች የበታች አመራርና ብዙኃን አባላት ዘንድ በተለይ “ሕገ-መንግሥታዊ ቀውሱንም” ሆነ በየአካባቢያቸው ያለውን ሕዝብ ብሶት ተከትሎ ውሎ-አድሮ የጎላ ልዩነት ሊኖር መቻሉ ላያከራክር ይችላል። የቀውስ ሁኔታ ከበረታ ከሕወሓት በስተቀር አንድነቱን ጠብቆ የሚዘልቅ የኢሕአዴግ አባል ድርጅት ላይኖር ይችላል። አንዳንዶቹ ከአመራሮቻቸው ቁጥጥርና ፍላጎት ውጭ ሠልፋቸውን ሊቀይሩ የማይችሉበት ምክንያት የለም። በዚኽ ረገድ በተለይ በአገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ሚና ቀላል አይሆንም።

ከምንም በላይ ይኽ ልዩነት ሊሰፋና አገርንና ሕዝብን ሊጠቅም በቻለ መልኩ አዲስ የኃይል አሠለፍ እንዲኖር የሚረዳው ግን ጠንካራ፣ ተአማኒነት ያለውና አስተማማኝ ምትክ የሚሆን ብሔራዊ አካል ሲቋቋም ወይም የዚኽ አካል እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከተቻለ ነው።

<u>*4ኛ. ያልታሰቡና ድንጋጤ የወለዳቸው ደንበር-ዘለል ቀስውሶች፤*</u>

*ማንኛውም የውስጥ ነውጥ አድፍጠው የቆዩና አጋጣሚን ለሚጠብቁ ክፍሎች ተደፋፍረው ድንገተኛ እርምጃ የመውሰድ ሁኔታን ይፈጥራል። በአሁኑ የአገራችን የመስክ ሁኔታ ይኽ ሁለት ገፅታዎች ያሉት ይመስለኛል። አንደኛው ማንኛውም ውጥረት የበዛበት መንግሥት አቅጣጫ ለማሣትና ጊዜ ለመግዛት የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠርና ያንንም በምክንያትነት ተጠቅሞ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የደረሱ ሕጎችን በማውጣት፣ አንዳንድ መሠረታዊ የሚባሉ የሕዝብ መብቶችን ሣይቀር በመገደብ የውስጥ ቁጥጥሩን ለማጠንከርና ሥልጣንን ለማቆየት ከሁሉ የተመረጠው መንገድ የውጭ ጦርነትን መጫር ስለሚሆን፣ በኢሕአዴግ በኩል በተለይ ከአቶ ኢሣኢያሷ ኤርትራ ጋር ቁርቁስ ሊጀምር ይችላል። ወይንም በውስጥ ያለን ችግር ለማባባስም ይሁን ማዕከላዊነት ሳልቷል በሚል ግምት በሸዓብያ በኩል ጥቃት ይሰለዘራል ብሎ ከማሰብና ያንን "አይቀሬ ወረራ" አስቀድሞ ለማክሸፍ በኢሕአዴግ በኩል የሚወሰድ እርምጃ ሊሆን ይችላል። ይኽ ድንገት የሚወሰድ እርምጃ ግን ከመብቶች መታፈን ውጭ አገሪቱን ወደ-ባሰ ቀውስ ሊወስድ ይችላል። ምናልባትም እንደ-ወደብ (የባሕር-በር) የመሣሰሉ የሕዝብን ብሔራዊ ስሜት የሚስቡና ሕዝብ የሚፈልጋቸውን ጥያቄዎች በማንሣት ለግጭቱ ሰበብ የሚሰጥበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል።*

*በአንፃሩ ይኽንን በመገመትም ይሁን ኢሕአዴግ ሚዛኑን እንዲያጣ ለማድረግ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ አለመረጋጋትን ለማባባስና ሁኔታውን ለመጠቀም በማሰብ በሸዓብያው የኤርትራ መንግሥት በኩል ተመሣሣይ የቀድሞ ማጥቃት ትንኮሣ ወይም ጠንከር ያለ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ይኽ ግን ከጊዚያዊ ጉዳት ውጭ የማታ-ማታ ጠቀሜታው ለኢሕአዴግ እንደሚሆን አያጠራጥርም።*

*የሆነ-ሆነ እንደዚኽ ዓይነቱ ልዕለ-ግቡ በደንብ ያልታሰበበትና ኃላፊነት የጎደለው የጀብደኝነት እርምጃ ለጊዚያዊ ሥልጣን ማቆያና የመበቃቀያ ተግባር እንጂ ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖ አገርን በሚጠቅም መልኩ ስለማይቋጭ ማንም ይጀምረው-ማን በተለይ በአሁኑ ጊዜ ለሁለቱም የማይጠቅምና ለውስጥ ቀውስ ተጨማሪ ከመሆንና ሕዝብን ወደ-ባሰ ችግር ከማስገባት የተለየ ውጤት አይኖረውም።*

*በተመሣሣይ ሁኔታ አንዳንድ አክራሪና ፅንፈኛ ክፍሎችም ይሁኑ ፀረ-አንድነት ኃይሎች ሁኑታውን ለማባባስና "መንግሥት ሚዛኑን እንዲስት" በማሰብ ሕዝብ የሥነ-ልቦና ጭንቀት ውስጥ እንዲገባና ሽብር እንዲለቅበት፣ በአገዛዙም ላይ ሕዝብ ይበልጥ ተስፋ እንዲቆርጥ በማስላት ከተራ-ሁከት-እስከ-አሰቃቂ-የጅምላ-ጭፍጨፋ በማድረግ ተግባር ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ። ይኽ ዓይነቱ ሽብርና ሰቆቃ ደግሞ በተለይ ሃይማኖትንና ጎሣን መሠረት እንዲያደርግም ጥረት እንደሚደረግ መገመት ይቻላል። ይኽ የሕዝባችንን ብሶትና የማዕከላዊነት መላላትን አጋጣሚ ተጠቅሞ የሚጫር ችግር በዜጎች ላይ ከሚያደርሰው አካላዊና ቁሣዊ ጉዳት በተጨማሪ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ጦስን የሚተውና የአንድነት፣ የእኩልነትና የፍትኅ ትግሉ ላይም የሚኖረው አሉታዊ ውጤት ማንም ከሚገምተው በላይ እንደሚሆን አያጠራጥርም።*

*ይበልጥ አሣዛኝ የሚሆነውና የዴሞክራሲ፣ የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግሉን እጅግ ወደ-ኋላ ሊወስደው የሚችለው ደግሞ ገና-ለገና ኢሕአዴግን ይጎዳ ይሆናል በሚል ግብዝ ስሊት በአንዳንድ ኢትዮጵያዊ ነን በሚሉ ድርጅቶች ዘንድ ከእንደዚኽ ዓይነት ኃይሎች ጋር በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ ለመተባበርና እገዛ ለማድረግ ወይም በዛመሞም እንኳን ቢሆን አብሮ ለመሰለፍ የሚወሰድ እርምጃ ይሆናል።*

*የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነና የኢትዮጵዊነትን ክብር አገዛዙን በምናይበት መነፅር ልናይ ከቶ ስለማይገባ በአገር አንድነትና በሕዝብ ሰላም ላይ የሚቃጡ ማናቸውንም እርምጃዎች እንደ-አንድ አገር ሕዝብ በጋራ መቆምና አደጋውን መከላከል የማንኛውም ዜጋ ግዴታ መሆኑ ምን-ጊዜም ሊዘነጋ አይገባም።*

<u>*5ኛ. "ሕገ-መንግሥታዊ" ቀውስ፣*</u>

*ላለፉት ሁለት አሥርተ-ዓመታት የአገራችንንና የሕዝቧን እጣ-ፈንታ እንዲወስኑ ሁኔታዎች የፈቀዱላቸው አቶ መለስ ሁሉም የመንግሥት የሥልጣን ዘርፎች ላይ ሙሉ ቁጥጥር ይዘው መቆየታቸውና ሥልጣናቸው ጠያቂና የበላይ የሌለበትና እንዲያውም ፍፁም ነው የሚባል እንደሆነ የብዙዎች ድምዳሜ ነው። የአገዛዛቸው ተፈጥሮአዊ ባኅሪ ጨርሶ የተለየ ቢሆንም አቶ መለስ በአገራችን ላይ የመጀመሪያው አምባ-ገነን ገዢ እንዳልሆኑ ግልጥ ነው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ላይ ያለው የአገዛዝ ሥርዓት የአንድ ድርጅት (ፓርቲ) ብቻ ሣይሆን የአንድ ግለ-ሰብ ፍፁም የበላይነት*

የሰፈነበት እንደሆነም ይታወቃል። አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ገና ከጅምሩ ገዥው ፖርቲ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአገራችንና በሕዝቧ ላይ የጫነውን “ሕገ-መንግሥት” የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓትን የሚነፍግ፣ የአገርና የሕዝብ አንድነትና ትሥሥር ላይ አሉታዊ ሁኔታዎችን የሚያመቻች፣ አቶ መለስና ድርጅታቸው ላለፉት ሃያ-አንድ ዓመታት የሚወቀሱባቸውን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ሁሉ 'አንቀፅ እየጠቀሱ' ማድረግ የሚያስችላቸው አፋኝና ስታሊናዊ፣ የአገሪቱንና የሕዝቧን መፃኢ-ዕድልም ከድርጅታቸውና ከመሪው ዕድሜ ጋር የተቆራኘ እንዲሆን ያደረገና ውጤቱም አደገኛ ክፍተትን የሚፈጥር ነው ያሉት ያለ-ምክንያት አልነበረም።

በኢሕአዴግ ደጋፊዎች በኩል የውስጥ ስሜታቸውን ማወቅ ባይቻልም በይፋ ግን የአቶ መለስን “የጤና-መታወክ” ተከትሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድም ይሁን በውጭው ዓለም ዘንድ በአገሪቱ ላይ የሚፈጠር የሥልጣን ክፍተት ሊያስከትል የሚችለውን ስጋት ለማስተባበልና ነገሮችን አቅልሎ ለማሣየት ጥረት እንደሚደረግ ግልጥ ነው። ለዚኽ ዓላማ “ደኅና ናቸው አገግመው ወደ-ሥራቸው በቅርብ ይመለሣሉ” ከሚለው ቀጥሎ የሚቀርበው የመጀመሪያ “የማረጋጊያ” ነጥብ 'አቶ መለስ በሥልጣናቸው መቀጠል የማይችሉበት ሁኔታ ቢኖርም እንኳን ኢሕአዴግ “በምርጫ” ሥልጣን የያዘ ድርጅት በመሆኑና “ለሕገ-መንግሥቱ” ተገዢ የሆነ የአገር መከላከያን ጨምሮ “በሕገ-መንግሥት” የተዋቀረ መንግሥታዊ ሥልጣን ስለ-መኖሩ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስን ጨምሮ “በምርጫ የሰየመ” ኢሕአዴግ የሚቆጣጠረው 'የሕዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት” እንዳለና ጠቅላይ-ሚኒስትሩን ተክተው የሚሠሩ ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር መኖራቸው፣ ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግም በመላ አገሪቱ መዋቅሩን የዘረጋና የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የሚችል ድርጅታዊ አቅም እንዳለው፣ ወዘተ..' ስለሆነም በአቶ መለስ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳይ ጊዚያዊ መደናገጥን ከመፍጠር ውጭ የሚያሰጋ ሁኔታ አይኖርም እንደሚባል ግልጥ ነው። በአንዳንድ “በጎ-አሣቢ” ወገኖችና በተለይም ትኩረታቸውን በአካባቢው መረጋጋት ላይ የጣሉ ክፍሎች ውጥረት እንዲቀንስና ሁኔታውም “ረገብ” ተደርጎ እንዲታይ ከማሰብ ይኸንኑ መሥመር የተከተሉ አስተያየቶችን መስጠታቸው የሚጠበቅ ነው።

አዎን ልክ ነው የተባሉት ሁሉ አሉ። ሆኖም ነገሩን ጠጋ ብሎ መመርመር ያስፈልጋል። እስኪ ሌላውን ትተን የምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩን ጉዳይ ከ“ሕገ-መንግሥቱ” አኳያ እንይ። በአገሪቱ “ሕገ-መንግሥት” አንቀፅ ሰባ-አምስት መሠረት በአሁኑ ጊዜ አቶ ኃይለ-ማርያም ደሣለኝ ከውጭ-ጉዳይ ሚኒስትርነታቸው በተጨማሪ የአገሪቱ ምክትል-ጠቅላይ-ሚንስትር ናቸው። በዚሁ አንቀፅ ቁጥር አንድ 'ሀ' ና 'ለ' መሠረት “በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጧቸውን ማናቸውንም ኃላፊነቶች መወጣት” እና “ጠቅላይ-ሚኒስትሩ በሌሉበት በእሣቸው ፈንታ” እንደሚሠሩ ተደንግጓል። ሆኖም የዚኹ አንቀፅ ቁጥር ሁለት “የምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ተጠሪነት ለጠቅላይ-ሚኒስትሩ ነው” ይላል። ይኽ ማለት ደግሞ ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ጤናን ጨምሮ በሚከሰቱ ልዩ-ልዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ሥልጣናቸው ላይ ካልሆኑና በሥልጣናቸው ላይ ሙሉ ቁጥጥር ከሌላቸው ወይም በሕይዎት ባይኖሩ ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ በቁጥር አንድ 'ሀ' ና 'ለ' ላይ የተቀመጡትን እነኝኽ የበላይ መሪነት የሥልጣን ኃላፊነቶች ጠቅላይ-ሚኒስትሩን ተክተው ለመሥራት ይቸገራሉ፤ አልፎም ሕጋዊ ዋስትና የላቸውም ማለት ነው።

ከላይ በማረጋጊያ መንፈስ የሚቀርቡ “ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና” በአብዛኛው ምኞታዊነት ያጠቃውና በተለይም እላይ የተዘረዘሩት “ማስተማመኛዎች” ሁሉ የቆሙበትን ኢሕአዴግአዊ “ሕገ-መንግሥት” ያሉትን ደካማ-ጎኖችና ሳንካዎች በቅጡ ያገናዘበ አይመስለኝም። ስለሆነም ነው አሁን ባለንበት ብዙዎችን ያስጨነቀ፣ ያሣሰበና የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ላይ ተስፋ-ሰጪ ሁኔታ አለመኖርና የአስተማማኝ ዋስትና እጦት ዋነኛ ተጠያቂ ከሆኑት ውስጥ አንዱ “ሕገ-መንግሥታዊ ቀውስ” ነው የምለው። ይኽ “ሕገ-መንግሥታዊ” ቀውስ የሚመነጨው ደግሞ ከራሱ ሥልጣንን ጠቅልሎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰጠው የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ነው።

በእነዚኽ ወገኖች አስተሣሰብ 'የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) ካለ (ያውም ከሞላ-ጎደል ሙሉ-በሙሉ በገዥው ፓርቲ አባላት የተሞላ)፣ በዚኽ አካል የተመረጡ ጠቅላይ-ሚኒስትር ካሉ፣ የእሣቸውም ረዳት የሆኑ ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር ካሉ፣ የሚኒስትሮች ምክር-ቤት ካለ፣ በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያሉ የአገር-መከላከያን፣ የፀጥታና የደኅንነቱን ኃይሎች ጨምሮ መንግሥታዊ መዋቅሮች ካሉ ነገሮች መሥመር ጠብቀው የማይሄዱበትና “ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ” ሊቀጥል የማይችልበት ምክንያት አይኖርም የሚል ነው።

በዚኽ “ሕገ-መንግሥት” ምዕራፍ 4 አንቀፅ 45 መሠረት “የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሥርዓተ-መንግሥት ፓርላሜንታዊ ነው” ይላል። አቶ መለስም በ“ሕገ-መንግሥቱ” አንቀፅ 73 ቁጥር 1 መሠረት በፓርላማ የተመረጡ ናቸው። አንቀፅ 50 ቁጥር 3 “የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት ነው”

ቢልም በአንቀፅ 72 እና አንቀፅ 74 መሠረት የመንግሥታዊ አስተዳደር ሥልጣኖች በሙሉ ለጠቅላይ-ሚኒስትሩ ተሰጥተዋል።

የአቶ መለስ ጤና ሁኔታ ኃላፊነቶቻቸውን መወጣት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ቢደርስ ወይም ለሕልፈተ-ሕይዎት ቢዳረጉ "ሕገ-መንግሥታዊ ቀውስ" የሚያስከትለው አንድም "ሕገ-መንግሥቱ" መንግሥታዊ ሥልጣንን ሙሉ-በሙሉ በእሣቸው እጅ ላይ የጣለ በመሆኑ፣ እሣቸውም ይኸንኑ "መብት" በማያወላዳ መልኩ እንኳን ከተቃዋሚዎቻቸው ከድርጅቶቻቸው (ከቀረው ሕወሓትም ሆነ የሱ ጭምብል ከሆነው ኢሕአዴግ) እና ከአጋሮቻቸው አስጊ ተቀናቃኝ እንዳይኖር አድርገው በሚገባ የተጠቀሙበትና ከእሣቸው በኋላ ስለሚኖር ሕጋዊ ተተኪም ጨርሶ ያልታሰበበት ይመስላል። የሚነገርለት የምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ጠቅላይ-ሚኒስትሩን <u>ተክቶ የመሥራት ጉዳይ የጠቅላይ-ሚኒስትሩን ሥልጣንና ኃላፊነት የማይመለከትና የማይጨምር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።</u>

ስለዚኽ አንደኛ፡- ምንም እንኳን የኢሕአዴግ "ሕገ-መንግሥት" አንቀፅ 75 ስለ-ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር ሥልጣንና ኃላፊነት ቢጠቀስም፣ በአንቀፅ 74 ቁጥር 2 ላይ ጠቅላይ-ሚኒስትሩ የሚኒስትሮች ምክር-ቤት አባላትን መርጦ ሹመታቸውን በምክር-ቤቱ ያስፀድቃል በሚለው ይጠቃለላል ካልተባለ በስተቀር ስለ ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር አሰያየም በተለየና በተብራራ መልኩ አልተጠቀሰም። ጠቅላይ-ሚኒስትሩ <u>ሙሉ-በሙሉ በሚቆጣጠሩት ፓርላማ</u> ከምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ጀምሮ ለማንኛውም መንግሥታዊ ኃላፊነት እንዲሾም ወስነው የሚያቀርቡትን ሰው ያለ አንዳች ጥያቄ ከመስማማት ውጭ እንደማይሆን ግልጥ ነው። ስለሆነም በአንቀፅ 50 ቁጥር 3 *"የፌዴራል መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል"* የተባለው ፓርላማ ሕግ-አስፈጻሚው ክፍል (ጠቅላይ-ሚኒስትሩ) የፈለገውን ለማድረግ የሚያስችለውና የሚጠቀምበት አካል ስለሆነ የሥልጣን ክፍፍል የሚባለው ይስሙላዊ እንደሆነ ግልጥ ነው።

በፓርላማዊ ሥርዓት በሚተዳደሩ ሌሎች አገሮች የሚገኙ ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሮች የሚመረጡት በፓርላማ ሲሆን ተጠሪነታቸውም ለፓርላማ ነው። በአሁኗ ኢትዮጵያ ግን በአንቀፅ 75 ቁጥር 2 በግልጥ እንደተቀመጠው የምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ተጠሪነት ለሾማቸው ለጠቅላይ-ሚኒስትሩ ነው። ያም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በሚሠራው ሕግ መሠረት የምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ ሥልጣን በጠቅላይ-ሚኒስትሩ በጎ-ፈቃድ ላይ ብቻ የተንጠለጠለና ጠቅላይ-ሚኒስትሩ በሥልጣን ላይ እስካለ ወይም ኃላፊነቶቹን መወጣት እስከቻለ ወይም ጊዚያዊ የጤና እክል ቢገጥመውም እንኳን በሕይዎት እስካለና ሥልጣኑ ላይ ያልተሸራረፈና ሙሉ ሥልጣን ሊኖረው ከቻለ ብቻ ነው።

ሁለተኛ፡- አቶ ኃይለ-ማርያም ደሣለኝ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር "በጣም የቀረበ የሥራ ግንኙነት" እንዳላቸውና ለአቶ መለስም "ፍፁም ታማኝ" መሆናቸው ከመነገሩና በዋናነት በእነዚሁ መለኪያዎች ምክንያትም አሁን ለያዙት የኃላፊነት ቦታ መብቃታቸው የብዙዎች እምነት በመሆኑ የእሣቸው የሥልጣን ዕድሜ በቀጥታ በአቶ መለስ ይሁንታና ከአቶ መለስ ሥልጣን ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይታመናል። ከዚኽ "ሕገ-መንግሥታዊ" ገደብ (እክል) በተጨማሪና ውጭ በአሁኑ ጊዜ ምክትል-ጠቅላይ ሚኒስትር ለሆኑት ለአቶ ኃይለ-ማርያም ደሣለኝ ነገሩን ይበልጥ አስቸጋሪ የሚያደርግባቸው አንድም የአውራው ፖርቲ የሕወሓት አባል አለመሆናቸው፣ ሌላም በሥልጣን ላይ ለመቆየትና ጫናቸውን ለማሳደር የሚያስችል፣ ሊያስፈራሩበትና ሊመኩበት የሚችል ድርጅታዊ አቅም የሌላቸው በመሆኑ ጭምር ነው። አቶ ኃይለ-ማርያም ሥልጣናቸውን የሚያረጋግጡበት ድርጅታዊ ደጀንም ይሁን መገልበጫ ስለሌላቸውም በያዙት ሥልጣን ለመቆየት የሚችሉበት "ሕጋዊ ዋስትናም" ሆነ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያሳችላቸው ኃይል የላቸውም። በመሆኑም፤ ምንም እንኳን በወታደሩ የሚታገዝ የሕወሓት ጉጅሌ ከጀርባ ሆኖ የሚባሉትን ብቻ እየፈፀሙ በጊዚያዊነት እንዲቆዩና የሚጠየቁትን አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ የመቻል ዕድል ቢኖርም፤ አቶ ኃይለ-ማርያም አቶ መለስን ተክተው በጠቅላይ-ሚኒስትርነት ሥልጣን ላይ ለመቆየትም ሆነ በጊዚያዊነትም እንኳን ቢሆን እንደ ጠቅላይ-ሚኒስትር ሙሉ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አይቻላቸውም ማለት ነው።

ሦስተኛ፤ "በሕገ-መንግሥቱ" ውስጥ ጠቅላይ-ሚኒስትሩ በልዩ-ልዩ ምክንያቶች ከሥልጣናቸው ቢነሱ፣ ወይም በሕይዎት ባይኖሩ አዲስ ጠቅላይ-ሚኒስትር እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚሰየም የተደነገገ ድንጋጌ የለም። በአዲስ ምርጫ በሚቋቋም አዲስ የተወካዮች ምክር-ቤት ነው ከተባለም ይኸንን የማድረግ ፓርላማ ምርጫ ምርጫ ሚገደነግገው ፓርላማው ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ያለውን ፓርላማ በትኖ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው በ"ሕገ-መንግሥቱ" አንቀፅ 60 መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው። ምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትሩ በሌለው የጠቅላይ-ሚኒስትር ሥልጣን ይኸንን ማድረግ አይችልም። በመሆኑም በአሁኑ ሁኔታ <u>የሥልጣን ሽግግርን የሚያረጋግጥ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና የለም።</u>

*አራተኛ፦- ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕይዎት ኖሮ በሚሰጥ ውሉን የውክልና ሥልጣን ካልሆነ በስተቀር ምክትል-ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአንቀፅ* 74 *ቁጥር* 1 *ላይ ለጠቅላይ-ሚኒስትሩ የተሰጠው ሥልጣን ስለማይኖረው የጦር-ኃይሎችና ሌሎች ቁልፍ መንግሥታዊ ተቋሞች ላይ ቁጥጥርም ሆነ የማዘዝ ሥልጣን አይኖረውም። ስለዚህ በአለው ሁኔታ የተለያዩ የመንግሥት ዘርፎች በምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር እዝና ቁጥጥር ሥር ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው። ይኽ ማለት ደግሞ የተለያዩ የእዝ-ሠንሰለቶችና "በመንግሥት ውስጥ መንግሥት" ሆነው የሚንቀሣቀሱ ክፍሎች ያሉት ስለሚሆን አንድ-ወጥ መንግሥታዊ አሠራር አይኖርም ማለት ነው።*
*በዚኽም ምክንያት ነው አቶ ኃይለማርያም ደሣለኝ 'ጥርሱ የወለቀና ክርኑ የደቀቀ' አንበሣ ሆነው የሚታዩት።*

*አምስተኛ፤ ምናልባት አንዳንድ ወገኖች የቀውስ ሁኔታዎችን ለመወጣት "አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ 'ሕገ-መንግሥቱ' እንዲሻሻል ማድረግና ለምክትል-ጠቅላይ-ሚኒስትር ኃይለ-ማርያም ሙሉ የተቅላይ-ሚኒስትርነት ሥልጣን መስጠት፣ ወይም ሌላ ሰው መምረጥ ይቻላል ሊሉ ይችላሉ። "አልሰሜን ግባ በለው" ካልሆነ በስተቀር አንቀፅ* 104 *እና አንቀፅ* 105 *ላይ በተቀመጠው መሠረት የኢሕአዴግ "ሕገ-መንግሥት" ሊሻሻል አይችልም። 'አራት-ነጥብ' የሚባለው የአቶ መለስ አባባል አግባብ የሚኖረው ይልቅ እዚኽ ላይ ነው።*

*መቼም ቢሆን ከሕግ-በላይ ሆኖ የቆየው ኢሕአዴግ ለራሱ "ሕገ-መንግሥት" በመገዛት የሚታማ አይደለም። የሚገርመው ግን እስከ-ዛሬ ድረስ ለሕዝብ መብቶች የሚታገሉ ዜጎችንና ድርጅቶችን "ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመናድ" በሚል ሲከስና ሲያንገላታ የኖረ ኢሕአዴግ እየገባ ያለበትን "ሕገ-መንግሥታዊ ቀውስ" በምን ሕግና እንዴት ሊወጣው እንደሚችል ነው።*

***ምን መደረግ ይኖርበታል፤***

*ከሁሉ በፊት በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች ከመደናገጥና ከወሬ ውዥንብር ሊርቁ ይገባ ይመስለኛል። "ወያኔ ሊወድቅ አንድ ሣምንት ቀረው" ዓይነት አመለካከትና እምነት ከንቱና አስገማች፣ አልፎም አዘናጊ ከመሆን አያልፍም። ከራሣችን ስሊትና ዕቅድ ውጭ የሚመጣን ለውጥ የምናስበውንና የምንፈልገውን ውጤት ይዞ እንዲወጣ ማድረጊ እጅግ ከባድ መሆኑ መታወቅ አለበት። ማንም ሞተ-ኖረ፣ ማንም ወጣ-ወረደ ጥያቄው ለመኖርና ለመሞቱም ሆነ ለመውጣት ለመውረዱ የኔ አስተዋፅዖና ሚና ምንድን ነው? የሚለው ነው። ይኽ ብቻ ግን አይደለም፣ ከዚያስ በቀጣዩ ሂደት ላይ የሚኖረኝ ቁጥጥር ወይም ወሣኝ አስተዋፅዖ ምንድነው? ብሎ መጠየቅና መልስ ማግኘት ያስፈልጋል። ድኅረ-ደርግ የነበረውን ሁኔታ ሕወሐት መቆጣጠር በመቻሉ የነገሮችን ሂደት እንደ-ፈለገው ለማሽከርከር ያገደው የለም። በአገሪቱ ቀጣይ ዕጣ-ፈንታ ላይ የጋራ አስተዋፅዖ እንዲኖር ከፈለግንና መፃዒ-ዕድላችን ላይ በጋራ ወሣኝ እንድንሆን ከፈለግን ወይም በጥቂቶች እንዲወሰንልን ካልፈለግን፣ ተባብረን ተነስተን አንድ ላይ መታገል ይኖርብናል።*

*የሚደረገው ትግል ለአገርና ለሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ኃላፊነት የሚሰማው ወገን ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ <u>ቢያንስ ቢያንስ አገራችንና ሕዝባችን ወደ-ባስ የቀውስ አዙሪት ውስጥ እንዳይገቡ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ይሆናል</u>። በገዥው ክፍል ባሉት በኩል አገራዊ ሰላምና መረጋጋት የሚታየው በሥልጣን ላይ ከመቆየት ነጠላ ስሌት በመነሣት ሊሆን ይችል ይሆናል። በአገር-ወዳዱና በዴሞክራቱ ኃይል በኩል አገራዊ ሰላምና መረጋጋት መታየት የሚኖርባቸው ከመልካም ሥርዓት ግንባታ ጋር ተጣምሮ ሊሆን ይገባል። አንዱ በሌላው ኪሣራ ሊገኝ እንደማይችል መገንዘብ ያስፈላጋል። በዴሞክራሲያዊው አገር-ወዳድና የአንድነት ኃይሉና በፀረ-አንድነት ኃይሎች መኻል ያለው አንዱ መሠረታዊ ልዩነት እዚኽ ላይ ነው።*

*በእርግጥ አገራዊ ሰላምና መረጋጋት ሣይኖር መልካም ሥርዓት ሊኖር አይችልም። ስለሆነም በተለይ ለለውጥ የሚታገለው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል በዚኽ ረገድ ኃላፊነቱን ለመወጣት በቅድሚያ እራሱን ብቁ አድርጎ መገኘት ይኖርበታል ማለት ነው። **ምን-ጊዜም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ በአገርና ሕዝብ ላይ የሚኖር ማንኛውም የቀውስ ሁኔታ ከገዥው ክፍል ይበልጥ ከባድ ፈተና ላይና አጣብቂኝ ውስጥ የሚጥለው ይኽን አገር-ወዳዱንና የዴሞክራሲውን ኃይል መሆኑን ነው።***

*በመሠረቱ ማንኛውም አጣብቂኝ ሁኔታ በውስጡ በጎና አስጊ መዘዞችን እንደሚያቅፍ መገንዘብ ይገባል። በውስጥና በውጭ ያሉ ነባራዊ ጭብጦች በሁለቱም ጎኖች ያለው ሁኔታ ላይ ጫናቸውን እንደሚያሳድሩም አጠያያቂ አይሆንም። በእንደዚኽ ዓይነት አጣብቂኝ ወቅት ያለው ዋናው ጥያቄ በሁለቱም በኩል ካሉ አዝማሚያዎች የትኛው ጎኑ እንዲከስምና የቱ አይሎ እንዲወጣ መወሰን የሚችለው አጠቃላይ የኃይል ሚዛን ጉዳይ ይሆናል።*

*በእንደዚኽ ዓይነት አጣብቂኝ ወቅት መስቀልኛ መንገድ ላይ የሚገኝን ኅብረተሰብና አገር ለአደጋ ከሚጋብዙ ሁኔታዎች መኻል የመጀመሪያው በቀጣዩ ላይ ዋስትና ማጣት፣ ወደፊት* (ቀጥሎ)

ምን እንደሚከተል እርግጠኛ አለመሆንና በመንግሥት አካላት ላይም ሆነ በተለዋጩ ላይ ሙሉ እምነት ማጣት ይሆናል፡፡ ለማንኛውም ኅብረተሰብ የፈታኝ ወቅትና የአጣብቂኝ ሁኔታ ትልቁ በሽታ የወደፊቱ አቅጣጫ ላይ በእርግጠኝነት "ይኸ ነው" ማለት አለመቻል ወይም አስተማማኝ ነገር፤ በተለይም በሰብዓዊ ደኅንነት ላይ ዋስትና ያለመኖር ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በዳበሩባቸውና ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት በሆነባቸው ኅብረተሰቦች አስተዳዳሪዎች (ድርጅቶችና ግለሰቦች) ቢቀያየሩም ከሞላ-ጎደል የኑሮ ሁኔታ ላይ እንጂ በአጠቃላይ የአገር አቅጣጫ ላይ ጥያቄ የሚነሣበት ሁኔታ በጣም ጥቂት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚኽ በላይ በአጭር-በአጭሩ ለማሣየት እንደሞከርኩት "ሕገ-መንግሥታዊ" ቀውስ በሚያስከትለው ውኸንብርም ሆነ "በገዥው ክበብ" መኻል ከሚኖር የሥልጣን ሽኩቻ፣ በገዥው አካልም ይሁን በውጭ ኃይሎች ከሚወሰዱ ያልታሰቡ (የድንጋጤ) ወይም ደንባሪ እርምጃዎች ሳቢያም ሆነ የቆዩና ያሉ የሕዝብ ብሶቶችን አስታኮ የሚፈጠርን ማንኛውም ክፍተት ለራሣቸው ግብ ለመጠቀም ከሚፈልጉ የውስጥም ሆነ የውጭ ፀረ-አንድነትም ሆኑ አክራሪ ኃይሎች በኩል በሚመነጩ ምክንያቶች ኅብረተሰባችንንና አገራችንን ወደ-አጉል አቅጣጫ ጎትተው የሚያስገቡና "ከድጡ-ወደ-ማጡ" ዓይነት የከፋ ሁኔታ ውስጥ የሚጨምሩ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

ይኽንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያውያን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚኽም፦

***አንደኛ፦ መሰባሰብ፤***

*ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵዊነትና በአገር-መውደድ መንፈስ ሊሰባሰቡ ይገባል፡፡ በተለይ ከአገር-ውጭ የሚገኘው ዜጋ በያለበት በ"ፀረ-ወያኔነት" ነጠላ መሥመር ሣይሆን በኢትዮጵያዊነት መንፈስና ለዚሁ ዓላማ መሰባሰብ ይኖርበታል፡፡ ኢትዮጵያውያን በያሉበት እየተሰባሰቡ "የአገር አንድነትና ብሔራዊ ክብር" ወይም "አገሬ-ክብሬ"፣ ወዘተ በሚል በኢትዮጵያዊነት መንፈስና ዓላማ ኮሚቴዎች ማቋቋም ተገቢ ይመስለኛል፡፡*

*ያለውን ያንዣበበ የቀውስ ሁኔታ ሰበብ በማድረግ ይኽንን መሰባሰብ ከአሁን በፊት አንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደታየው የፀረ-አንድነትና ፀረ-ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ቡድኖች መድረክና መንኻሪያ እንዲሆን በንም ዓይነት መፈቀድ አይኖርበትም፡፡ የትም ቦታ የሚደረግ መሰባሰብ በአንዲት አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሥርና በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ የሚገለፅ የትግል አጋርነት ካለም አጋርነቱ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ለፍትኅና ለእኩልነት ለተሠለፉና ከተሠለፉ ክፍሎች ጋር ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ እዚኽ ላይ ምንም ብዥታ ሊኖርና ውሎ-አድሮ ሕዝብና አገርን ለሚጎዱ ክፍሎች አስተዋፅዖ አድራጊና የሌሎች አጀንዳ ማሚያ መሆን አይገባም፡፡*

***ሁለተኛ፦ ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ መፍጠር፤***

*ቀደም-ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የፈለግነውን ያኽል በጎ ብንመኝ፣ አገዛዙ ምን ቢፈረካከስ፣ ሁኔታዎች ምን ያኽል ለለውጥ አመቺ ቢሆኑ አገር-አቀፍ አደረጃጀት ከሌለን ማንኛውም የሚመጣ ለውጥ ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት መሆኑ ሲበዛ አጠራጣሪ ነው፡፡ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሣጠርም ይሁን አስገድዶ ወደ ድርድር እንዲመጣ ለማድረግ፣ ሕዝባችንን ከቀጣይ ሰቆቃ ለማዳንም ሆነ በአገራችን አንድነትና ሰላም ላይ ያለንን ስጋት ለማስወገድ፣ ወዘተ.. ከአቶ መለስ መታመምም ሆነ በሕይዎት መኖር-አለመኖር ይበልጥና ከሁሉም በላይና የተሻለ አስተማማኙ ለውጥ-ፈላጊው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገን ጊዜ ሣይፈጅ ብቁና ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው፡፡ ይኽንን አደገኛ ክፍተት መሙላቱም በሁሉም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ዘንድ የአጀንዳዎች ሁሉ ቀዳሚ ሊሆን ይገባል፡፡ ይኽንን ማድረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡*

- *ጠንካራ የአንድነት ኃይል በመፍጠር ልዩነቶችን መሠረት ባደረገ መልኩ ሁኔታዎች ተባብሰው አገራችን ወደ-አደገኛ ትርምስ እንዳትሄድ ይረዳል፡፡*
- *በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የኃይል መሰባሰብ ከተደረገና ለሕዝባችን ሁነኛ አለኝታ መሆን ከተቻለ፣ ሕዝባችን መልሶ የትግሉ ማዕከል ሊሆንና ለሥርዓት-ለውጥ የሚደረገውን ትግል መልክ ለማስያዝና የተስፋ-መቁረጡና የትጥቅ-መፍታቱ አባዜ እንዲወገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ በተለይ ተስፋው እየተሟጠጠ፣ ቅስሙ እየተሰበረና አማራጭ ከማጣት የተነሣ ሣይወድ ዕንፈኞችን መቀላቀልና በራሱ ዘለቄታዊ ጥቅም ላይ እንዲዘምት ግድ ሊሆንበት ለሚችለው ወጣት ክፍል የወደፊት ዕጣ-ፈንታውን በበጎው መወሰን የሚያስችለው የትግል መድረክ ይሆንለታል፡፡*

- ይኸ ሲሆን ደግሞ ለአገሪቱና ለሕዝቧ ዘለቄታዊ ጥቅም የቆሙ ወገኖች በአገዛዙ ዙሪያ ያሉ ጭምር የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስለሚያገኙት የዴሞክራሲውን ጎራ ለማጠናከር ዕድል ይሰጣል፡፡
- በአገሪቱ ላይ የተፈጠረውን አደገኛ ክፍተት መድፈን ሲቻል ሕዝባችን በወደፊቱ የአገሪቱ ዕድልና አቅጣጫ ላይ ከሚኖረው ሥነ-ልቦናዊ ጭንቀትና ስጋት ይድናል፡፡ ይኸም አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡
- በአገራችን ጉዳይ እጃቸውን ያስገቡና አንድ-ጎንዮሽ ድጋፋቸውን ለኢሕአዴግ ሲሰጡ በቆዩ ክፍሎች ዘንድ ተከብሮ ተቀባይነትን ማትረፍና አገሪቱ ሁነኛ አማራጭ እንዳላት፣ የሚሰጡት ድጋፍም ጭፍንና ደፈናዊ እንዳይሆን ማድረግ ያስችላል፡፡
- በአገዛዙ ሥር ላሉ የአገር መከላከያን ለመሰሉ መንግሥታዊ መዋቅሮች አባላት መሠረት-የሌለው ስጋትን ሊያስወግድና እንደ-አንዲት-አገር-ዜጎች ለመተያየት የተሻለ መተማመንን ይፈጥራል፡፡
- አገዛዙ የሚከተላቸውን የጥፋት ፖሊሲዎች እንዳይገፋባቸው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጫናዎችን ማሳደር ያስችላል፡፡
- የተለያዩ ፀረ-አንድነትና አክራሪ ቡድኖችን በመርዳት አገርን ለመበተንና የሕዝብን ሰላም ለመበጥበጥ የተሠለፉ ባዕዳን ኃይሎች በተቃዋሚው ጎራ ያሉ የተወሰኑ ወገኖችን በመሣሪያነት እንዳይጠቀሙባቸው አስተዋፅዖና ጫና ለማድረግ ይረዳል፡፡
- ለገዛዙ ኃላፊዎችና አባላት በተለይም የአገራቸውና የሕዝባቸውን ዘለቄታዊ ጥቅም ለሚያስቀድሙ ወገኖች ለሥርዓት ለውጥ የሚደረገው ትግል የአንዲትን አገር ዜጎች በአጥፊና-ጠፊ ሊያሰልፍ እንደማይገባና ለጋራ አገራችን ችግሮች የጋራ መፍትሔ መፈለግ እንደሚቻል ተከባብሮ ለመደማመጥ ዕድል ይሰጣል፡፡ ይኸ ሁኔታ ደግሞ በአገራችን ብሔራዊ የእርቅና-ሰላም ሂደትን በተከተለ መንፈስ የሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሠረት ለመጣል የተሻለ አስተማማኝ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡
- ይኸ ሁነኛ ብሔራዊ ኃይል ከወዲኹ በመንግሥት ደረጃ ተደራጅቶ እንደ-መንግሥትም የሚሠራና የሚንቀሣቀስ ስለሚሆን የቀውስ ሁኔታ በአገሪቱ ላይ ቢፈጠር የማዕከላዊነት ክፍተት አይኖርም፡፡ ለምሣሌ በአሁኑ ጊዜ ሊከሰት ይችላል የሚባለው በገዥው ክፍል መኻል መፈረካከስ ቢፈጠር እንኳን የዚኸ ዓይነት ብሔራዊ ኃይል ካለ ሕዝባዊነት ካላቸው የአገዛዙ ክፍሎች ጋር በመሆንም ሆነ እራሱን ችሎ አገራዊ ኃላፊነትን በመረከብ የማዕከላዊነት ክፍተት እንዳይኖር ማድረግ ይቻላል፡፡

(ከአሁን በፊት እንዳልኩት *ስለዚኸ አካል አመሠራረትና አሠራር በአስፈላጊው ጊዜ በተለዬ እንደማቀብ አሣውቃለሁ፡፡)*

አልበርት አንሽታይን እንዳለው ማንኛውም አሉታዊና አደጋን ሊጋብዝ የሚችል ሁኔታ መልካም አጋጣሚንም በውስጡ የያዘ በመሆኑ ከአቶ መለስ የጤና መታወክ ተስታኮ የተከሰተው ሁኔታ ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው አገራችንንና ሕዝባችንን ታሪካዊ መስቀልኛ መንገድ ላይ ስለጣለ፤ በገዥው ፓርቲ ያለውም ሆነ እሱን ለመጣል በሚታገለው ወገን በኩል የቅድሚያ-ቅድሚያ ተሰጥቶት ከልብ ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ በልዩ-ልዩ ጎራ ሊያሰልፉንና በአገራችን በሰፈነው ሁኔታ ተያይዞ መጥፋትን ብቻ ሊያስከትል ከሚችል ከግለ-ሰብም ሆነ ከቡድን፣ ከድርጅትም ሆነ ከጎሣና አካባቢ፣ ከፖለቲካ ርእዮትም ሆነ ከመንፈሣዊ እምነት በላይ የሁሉም ዜጎቿ የጋራ ቤት የሆነችውና የሁሉም ጥቅም ሊከበርባት የሚችል ውድ አገረ-ኢትዮጵያን ማስቀደም እንደሚገባ ነው፡፡ አንዱ በሌላው መቃብር ላይ ሊመሠርተው የሚችልም ሆነ ሊያስጠብቀው የሚችል ጥቅም የለም፡፡ ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ ወገኖቹን ለማሳሰብ እንደሞከርኩት ሁሉ አሁንም ቢሆን ለሁላችን ሊጠቅም የሚችልና ፍትኅን፣ እኩልነትንና አንድነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲኖር ከፈለግን፣ በአባት-እናቶቻችን ደምና አጥንት በብዙ መስዋዕትነት የተገነባው አንድነታችን ተከብሮ ማየት ከፈለግን፣ የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት ብቻ ሣንሆን እንኳን ለእኛ ለኢትዮጵያን ለቀረውም አፍሪቃዊ ወገናችን የሰላምና የብልፅግና ተምሣሌት መሆን ከፈለግንና ኢትዮጵያውያን የተቀደሰች አገራቸው ሲያል ሆናባቸው የሚሸሿት ሳትሆን የወጡ በጉጉት ተመልሰው ሊኖሩባት የሚሽቀዳደሙባት እንድትሆን ከፈለግን፣ ዜጎቻችንን ከወራዳ ስደትና ከቁም-ስቃይ እንዲድኑ ከልብ ካሰብን አሁንም ሆነ ምን-ጊዜም አስተሣሰባችን ኢትዮጵያዊ፣ የፖለቲካ ቅኝታችን ኢትዮጵያዊነት፣ አሠላለፋችን በአንድነት ሊሆን ይገባል፡፡ ይኸ ሊሆን የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ በእርግጥ ይቻላል!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለኢትዮጵያዊነት!!